# ጥብቅ ማሳሰቢያ ቀዳሚ እርምጃ !!!

ለሁሉም በፍጥነት ይዳረስ መፍትሄም ይበጅለት!

-የዕገዳ አዋጁን ተከትሎ ህወኃት በጎንደርና በጎጃም ህዝብ ላይ ያነጣጠረ የተቀናጀ ትጥቅ የማስፈታትና የመሰብሰብ ዘመቻ ጀምሯል።

-ይህ ጎጃምን እና ጎንደርን በልዩ ዕቅድ ትጥቅ የማስፈታት ልዩ ዘመቻ እንቅፋቶች እንዳይገጥሙ በማሰብ ዘመቻው ከማዕከል በተመደቡ ጀኔራሎችና የደህንነት ሹሞች( በመከላከያ ዘመቻ ኃላፊው ጀ/ል ገብረግዛብሄር ሙብራቱና በደህንነት ቢሮው ም/ኃላፊ ያሬድ ህሉፍ) ባህርዳር ላይ በተመሰረተ ማዘዣ ጣቢያ በቅርብ የሚታዘዝ ሁኖ በአለቃ ፀጋየ የሚመራ ዘመቻ ነው።

-ሁሉንም የጎንደርና የጎጃምን ቦታወች ገምግመው ከባድ፤ መካከለኛና ቀላል ብለው ደረጃ ሰጥተዋቸዋል። ትጥቅ የማስፈታቱ ጊዜ በ 3 ዙር ለማካሄድ ያቀዱ ሲሆን የዓመቱ ዋነኛ ተግባር አድርገውታል። የኃይል ምደባቸውም ይህንኑ ታሳቢ ያደረገ ሲሆን የየአካባቢው ታጣቂወችንም መጀመሪያ ያሳትፏቸዋል በመጨረሻም የነሱም ትጥቅ ይቀነሳል።

-በየከተሞች የተተከሉ የሳተላይት ዲሾችን ቀድሞ ማውደም፤ የኢንተርኔትና የስልክ አገልግሎቶችንም ኔትወርክ ማወክ ጭምር እርምጃ እንደሚወሰድ ታቅዷል።

-በትጥቅ ማስፈታት ዘመቻው የሚያጋጥሙትን እንቅፋቶች ለማስወገድ ኃይል እንዲጠቀሙና ተያያዥ ንብረቶችንም እንዲወረሱ ለወራሪ ኃይሉ ስልጣን ተሰጥቶታል።
ይህ መረጃ ከትላንት ጀምሮ በስፋት እየተወራ ያለ ቢሆንም ፤ እኔም የበኩሌን ጥረት አድርጌ ያረጋገጥኩት ነው።
መፍትሄ
-በጉዳዩ ላይ ህዝቡን ማንቃት፤ በተለይ የጎጃምና የጎንደር ህዝብ የገጠሩም የከተማውም መረጃው በፍጥነት እንዲደርሰው ማድረግ።
-በውጭ የሚኖረው ህዝብም መረጃውን በትጋት የማዳረስና በጉዳዩ ላይ መወያየት ሂደቱንም በትኩረት መከታተል ይኖርበታል።

-እየተካሄደ ያለውን ህዝባዊ ተጋድሎ አጠናክሮ መቀጠልና በየአካባቢው መንገዶችን የመዝጋት እርምጃ ማጠናከር።

- ለህውኃት ወራሪ ኃይል የሚጠቁምና የሚተባበር ባንዳ ላይ ቀዳሚ እርምጃ መውሰድ።

-ህዝባዊ ተጋድሎውን በሁሉም የአገሪቱ ከባቢወች በሁሉም ተቋአሞች ትግሉን እንደአዲስ ደረጃውን ከፍ አድርጎ ማቀጣጠል ዩኒቨርስቲወችን ትምህርት ቤቶችን እና የትራንስፖርት ዘርፎችን ጭምር በስፋት የተጋድሎው አካል ማድረግ።

# ሌላም ሃሳብ ተጨማምሮበት፤ በጉዳዩ ላይ ትኩረት አድርጋችሁ የምትሰሩ የፖለቲካ ድርጅቶች፤ ሲቪክ ማህበራት፤ ሚዲያወችና የአማራ ተጋድሎ አስተባባሪወች ችግሩን በቀዳሚነት ልትይዙት ይገባል።

Gabriel B.